# ምዕራፍ ዘጠኝ

## መረጃ አያያዝ እና ድርድር

### መረጃ አያያዝ እና ድርድር

**ተግባር 9.1**

ተማሪዎች የአዝርዕት ዓይነቶችን፣ የጓሮ አትክልት ዓይነቶችን፣ የቤት ውስጥ እቃዎችን ዘርዝሩ፡፡ የሚመሳሰሉትን በአንድ ላይ በመዘርዘር መድቧቸው፡፡ የሚመሳሰሉበትን መንገድ አብራሩ፡፡

### 9.1. ቀላል መረጃዎችን መሰብሰብ

ተማሪዎች መረጃዎችን ስታደራጁ ቀላሉ መንገድ በዓይነታቸው፣ በመጠናቸው፣ በተሰሩበት ቁስ ወይም በባህሪያቸው የሚመሳሰሉ መሆን አለበት፡፡

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ምደብ 1 (ፍራፍሬዎች) | ሎሚ | ብርቱካን | ሙዝ | ማንጎ | ፓፓዬ | አናናስ |
| ምድብ 2 (አዝርዕት) | ባቄላ | ስንዴ | ማሽላ | ሽምብራ | ጤፍ | በቆሎ |

**የቡድን ሥራ**

በአንድ መኖሪያ ቤት ውስጥ የሚገኙ መገልገያ መሳሪያዎችን በመዘርዘር ከእንጨት የተሰሩ፣ ከሸክላ (ከአፈር) የተሰሩ፣ ከብረት የተሰሩ እና ከእንጨትና ከብረት ጥምረት የተሰሩ በማለት በምሳሌው መሠረት ሙሉ፡፡

| ምደብ 1 | ምድብ 2 | ምድብ 3 | ምድብ 4 |
|---|---|---|---|
| ከእንጨት የተሰሩ | ከሸክላ የተሰሩ | ከብረት የተሰሩ | ከእንጨትና ከብረት በጥምረት የተሰሩ |
| • ጠረጴዛ<br>• __________<br>• __________<br>• __________<br>• __________ | ሸክላ ድስት<br>__________<br>__________<br>__________<br>__________ | የብረት ድስት<br>__________<br>__________<br>__________<br>__________ | መዶሻ<br>__________<br>__________<br>__________ |

## መልመጃ-9 ሀ

1. በክፍላችሁ ውስጥ የሚገኙ ወንድና ሴት ተማሪዎችን በመለየትና በስም በመዘርዘር በሁለት ምድብ መድቡ::
2. በክፍላችሁ ውስጥ የሚገኙትን ቁሳቁሶች ጎነ አራት፣ ጎነ ሦስት እና የክብ ቅርጽ ያላቸውን በመዘርዘር በሦስት ቦታ መድቡ::
3. የሚከተሉትን የእንስሳት ዝርዝር በማጤን መድቡ፤ ሠንጠረዡንም ሙሉ::

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አንበሳ | ውሻ | በግ | ዋልያ | ድመት | ወፍ |
| ዝንጀሮ | ላም | በቅሎ | ቀይ ቀበሮ | ዶሮ | |
| ዝሆን | ነብር | ጎሽ | በሬ | አሞራ | |
| ጦጣ | አነር | ሚዳቋ | ፈረስ | አህያ | |

| የቤት እንስሳት | የዱር እንስሳት | በክንፍ በሪሪ |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

Ethiopia republished

## 9.2. የቀላል መረጃ ሰንጠረዥ

### ተግባር 9.2

1. ተማሪዎች የአናጺ፣የህክምና እና የግብርና ባለሙያዎች ሥራቸውን ለማከናወን የሚጠቀሙባቸውን መሳሪያዎች በመዘርዘር መድቧቸው::
2. እናንተ ለትምህርት የሚያስፈልጓችሁን መሳሪያዎች ዘርዝሩ:: ከዘረዘራችሁ በኋላ በሦስት በተለያዩ ምድቦች ለመመደብ ሞክሩ::

ምሳሌ:-


የቁም መጥረጊያ


መዶሻ


ቁልፍ


ፊሽካ


እስኪርቢቶ


አካፋ


ደወል


መጋዝ


እርሳስ

እነዚህን መሳሪያዎች በቀላሉ በመረጃ ሰንጠረዥ እናስቀምጣቸው፡፡ የህንፃ መሳሪያዎች እና የትምህርት መሳሪያ ዕቃዎች በማለት በሰንጠረዡ አሳዩ::

| የህንፃ መሳሪያ | የትምህርት መሳሪያዎች |
|---|---|
| • ቁልፍ | • እስኪርፕቶ |
| • መዶሻ | • እርሳስ |
| • የቁም መጥረጊያ | • ደወል |
| • መጋዝ | • ፊሽካ |
| • አካፋ | |

## መልመጃ-9 ሀ

***በምሳሌው መሠረት መድቡ፡፡***

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቁሶች ፈሳሽና ጠጣር በማለት በሠንጠረዥ አደራጁ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ወተት | ውኃ | ግድግዳ | ድንጋይ |
| ባትሪ ድንጋይ | ዘይት | ወንበር | መዶሻ |

2. ቀጥሎ የተሰጡት የቁሳቁሶች ዝርዝር ከሥር በተሰጠው ሠንጠረዥ አደራጁ፡፡

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| - እንቁላል | - ወተት | - ምስር | - ባቄላ | - በቆሎ | - በርበሬ | - ድንች |
| - ስጋ | - ሽንኩርት | - ስንዴ | - ጕመን | - ቲማቲም | - ብርቱካን | - |
| - መፅሐፍ | - ወንበር | - ደብተር | - እስኪርቢቶ | - ጠመኔ | | |

| ጥራጥሬ | የእንስሳት ተዋፅኦ | የፅሕፈት መሳሪያዎች | የጓሮ አትክልት |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

# 9.3 የቁጥሮችና የቅርፃ ቅርጾች ቀላል ድርድር

**ተግባር 9.3**

1. ተማሪዎች የቁጥሮችን ቅደም ተከተል ሁለት ሁለት በመዝለል መግለጽ ትችላላችሁን?
2. የሚከተሉትን ቅርጾች ድርድር በመመልከት ክፍት ቦታዎችን ሙሉ::



______፣______፣ _____

- የቁጥሮችንና የቅርፃ ቅርጾችን ቀላል ድርድር እንደ አጀማመራቸው በመመልከትና በማጤን መደርደር ይቻላል::

**ለምሳሌ:-**



_____፣ _____ ፣____ባዶ ቦታውን ሙሉ::

መፍትሔው 

**መልመጃ-9 ሐ**

*I. የሚከተሉትን ነገሮች ቀላል ድርድር በማጥናት ባዶ ቦታውን ሙሉ ወይም ቀቡ::*

ሀ.  __________፣__________፣__________፣________::

ለ. 2፣ 4፣ 6፣______፣ ______፣______፣14፣______ ፣______፣20

ሐ. 0፣ 3፣ 6፣ 9፣ ___________፣__________፣ 18፣ 21፣ ___________፣ 27

መ.  ፣______፣______፣______::

ሠ.  ______፣______፣______::

ረ. 

__________፣ __________ ፣__________፣

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

# የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ

**ሀ. ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. ሁሉም የቤት ውስጥ እቃዎች ተመሳሳይ አገልግሎት አላቸው።
2. የተለያዩ መረጃዎችን ስናሰባስብ በአንድ ቦታ ማከማቸት ጠቃሚ ነው።
3. መረጃዎችን በመጠናቸው፣ በአይነታቸውና በባህሪያቸው ለይቶ ማደራጀት ጠቃሚ ነው።
4. ቀላል መረጃዎችን በሰንጠረዥ ማደራጀቱ ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው።
5. የተለያዩ ቀርጽ ያላቸውን ቁሶች በየቅርፃቸው መደርደር አስፈላጊ ነው።

**ለ. የሚከተሉትን የቁጥርና የቅርፃቅርጽ ድርድር ወይም ፓተርን አሟሉ።**

1. 0፣ 4፣ 8፣ ________፣ ______፣ 20፣ 24፣ ________፣ 32፣ 36፣ _____፣ 44

2.  ________፣ ____________።

 ________፣ ____፣ ____፣ ____።

**ሐ. የሚከተሉትን ነገሮች ባህሪይ በማጤን መድቡአቸው፣ በሠንጠረዥም አሳዩ።**

| | | |
|---|---|---|
| ብርቱካን | ፓስታ | ትርንጎ |
| በቅሎ | መኮረኒ | አቡካዶ |
| መንደሪን | ሩዝ | በግ |
| ፍየል | ሙዝ | ስኳር |
| ዶሮ | ፓፓያ | ጨው |